# የክርስትያን ባህርይ(6)

## <u>ጥናት አንድ (ሮሜ 3፥9-26)</u>

የጥናቱ ዓላማ፡- እግዚአብሄር ለምን እንደተቀበለን በመረዳት ስለራሳችንና ስለሌሎች ሰዎች የሚኖረንን አመለካከት ለመቀየር።

የጥናት መክፈቻ፡- በአካባቢህ ያሉ ሰዎች እንዲቀበሉህ በማለት ያደረዛቸው ነገሮች አሉ ወይ? ለምን ይመስልሃል በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት ሰዎች የምንሞክረው?

1. ሮሜ 3፥9-26 ይነበብ። በቁጥር 10-18 ፍጥረት ሁሉ ከሃጥያት በታች እንደሆነ ያሳያል። በዚህ ጥቅስና አንተ ስለሰዎች ስላለህ አመለካከት መሃል ምን ልዩነት ታያለህ?
2. በቁጥር 13-18 የሰውነት ክፍሎችን በመጥቀስ ሃጥያት ምን ያህል የሚያህል እንደበከለን የሚያሳየን እንዴት ነው?
3. ቁጥር 9-20 ያለው ክፍል ስለሰው ልጆች ግብረገባዊና መንፈሳዊ ሁኔታ ምን ያስረዳናል?
4. የነበርንበት መንፈሳዊ ሁኔታና በቁጥር 24 ያገኘነው ጽድቅ ሲታይ መጽደቃችን ለምንድነው አስደናቂ ነገር የሚሆነው።
5. እግዚአብሄር ለእኛ የሰራውን ሁሉ በትክክል መረዳታችን ስለራሳችን የሚኖረንን አመለካከት እንዴት ይቀይረዋል?
6. ቤዛነት (ቁ 4) የሚለው ቃል ባርያን ከባርነቱ መግዛት ማለት ነው። እኛ ከማመናችን በፊት ባርያዎች ለመባል የቻልንበትን ምክንያት አስረዳ።
7. ሰው በክርስቶስ ካመነስ በኋላ እስረኛ ሊያደርጉት የሚችሉ ነገሮች ያሉ ይመስልሃል ወይ? ምሳሌ ስጥ።
8. በእግዚአብሄር ይቅር መባላችን እርስ በእርሳችን ላለን ግንኙነት ምን አስተዋጽዖ ያደርጋል ትላለህ? በመለስከው መልስ መሰረት በዚህ ሳምንት በሕይወትህ በሥራ ላይ ልታውለው በጌታ ፊት ፀልይና ውሳኔ አድርግ።

## ጥናት ሁለት (ቆላስያስ 1፥15-23)

**የጥናቱ ዓላማ፡- የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነትና ሥራውን በጥልቀት ለመረዳት። የጥናት መክፈቻ፡- ጌታን እንደግል መድሐኒትህ ከመቀበልህ በፊት ክርስቶስን የምትመለከተው እንዴት እንደነበረ ለመግለጽ ሞክር።**

1. ቆላስያስ 1፥15-23ትን በአንድነት በማንበብ ስለክርስቶስ የትኛው ክፍል ነው ለአንተ አስደናቂ ሆኖ የታየህ?
2. ቁ 15 "እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው" ይላል። ከእግዚአብሄር አለመታየትና አንተ እርሱን ለማወቅ ብሎም ህብረት ለማድረግ በምታደርገው ጥረት የምትቸገርባቸው ነገሮች አሉ ወይ? እነዚህስ ነገሮች ምንድናቸው?
3. ከላይ ችግር ተብለው ለተዘረዘሩት ነገሮች የክርስቶስ ሥጋን መልበስና መምጣት ምን ያህል መልስ ይሆንሃል?
4. በቁ 16-20 መሠረት የክርስቶስ ጌትነትና የበላይነት የተጠቀሱበትን መንገዶች ዘርዝር።
5. በቁ 16 መሠረት ፍጥረት ሁሉ የተፈጠረው ለምንድነው ይላል? ይህ አባባል ስለህይወት፥ ስላከማቸናቸው ነገሮች፥ ስለግንኙነትና ስለመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ ምን ያስተምረናል?
6. ቁጥር 20ን በማንበብ እግዚአብሄር ለዓለም ሁሉ ስላለው አጠቃላይ እቅድ ምን ትማራለህ?
7. በዕቅዱ ውስጥ እንድንሳተፍ እግዚአብሄር ለእኛ ለሰዎች ያደረገው ነገር ምንድነው? (ቁ 21-22) ከእኛስ ምን ይጠብቃል? (ቁ 23)
8. ቁጥር 23 ትን ስታነብ በእምነትህ እንድትታነጽና ጸንተህ በያዝከው የወንጌል እውነት እንድትቆም ምን ያህል ያበረታታሃል? ራስህንስ ለክርስቶስ ጌትነት ለማስገዛት ምን ያህል ፈቃደኛና ዝግጁ መሆንህን በዚህ ትምህርት ራስህን መርምር።

# <u>ጥናት ሶስት (ሉቃስ 14፥25-35)</u>

*የጥናቱ ዓላማ፡- የደቀመዛሙርቱን ትልቅ ሃላፊነት በመማር በሕይወታችን መሥዋዕትነት የሞላው ተጨባጭ ለውጥ እንዲታይ ለማበረታታት።*

*የጥናት መክፈቻ፡- የተለያዩ ሰዎች ወደ ክርስቶስ ለተለያዩ ምክንያቶች ይመጣሉ። አንተንስ በመጀመሪያ ወደ ክርስቶስ የሳበህ ዋነኛ ነገር ምን ነበረ?*

1. ሉቃስ 14፥25-35 በህብረት ይነበብ። በቁጥር 25-27 ኢየሱስ ከተከታዮቹ ምን እንደሚጠብቅ ነው የሚነግራቸው?
2. ቁጥር 26 ላይ “መጥላት” የሚለውን ቃል በምን መንገድ ነው መረዳት ያለብን የሚመስልህ? (ቤተሰብንና የራስን ሕይወት ከመጥላት አንፃር)
3. በመጀመሪያው ምዕተዓለም ሰው መስቀል ተሸከመ ማለት እንደሚሞት የተረጋገጠ ነበረ። በዚህ ዓይን ቁ 27 ለአንተ የሚሰጥህን ትርጉም ግለጽ።
4. ቁ 28-30 ቤት ስትሰራ ማሰብ የሚኖርብህ ነገሮች ምን ምንድናቸው? ሕንጻውን ለመጨረስ ሊያግዱህ የሚችሉትን ነገሮች ዘርዝር።
5. የንጉሡና የህንጻ ሰራተኛው ምሳሌ በምን ዓይነት ነው የኢየሱስን ሃሳብ ሊገልጹ የሚችሉት?
6. በአዲስ ኪዳን ዘመን ጨው ምግብ እንዳይበላሽ ይገለገሉበት ነበረ። በምን ዓይነት መንገድ ነው ይህ ከደቀመዛሙርትነት ሥራችን ጋራ የሚነጻጸረው? ቁ 34-35
7. የደቀመዛሙርትነታቸውን ተግባር ለመፈጸም ሙሉ በሙሉ አለመሰጠታቸውን ሰዎች የሚገልጡባቸው መንገዶች ምንድናቸው? ጨውነቱን ካጣ ጨው ጋራስ የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?
8. ክርስቶስን መከተል በህይወትህ ትልቅ ዋጋ የሚያስከፍል ሆኖ ያገኘህበትን ነገር አካፍል። (በትምህርት፥ በሥራ፥ በግንኙነት፥ ወዘተ)
9. ዛሬ በህይወትህ የኢየሱስ ደቀመዝሙር ከመሆንህ የተነሳ መቀየር ያለብህን ነገር በማሰብ በጌታ ፊት የጸሎት ርዕስህ አድርገው።

<u>ጥናት አራት(ዘፍጥረት 39፥1-23)</u>

የጥናቱ ዓላማ፡-

የጥናት መክፈቻ፡- በክርስትና ህይወት "ፈተና" የሚለውን ቃል እንዴት ትረዳዋለህ? በህይወትህስ ተለማምደኸው ታውቃለህ ወይ?

1. ዘፍጥረት 39፥1-23 በአንድነት ይነበብ። በዚህ ምንባብ ውስጥ ተዋናኞች እነማን ናቸው? ስለእያንዳንዱ በአጭር አረፍተነገር ማንነታቸውን አስረዳ።
2. ዮሴፍ ያለፈበትን ሁኔታ ከምንባቡ ተመልክተሃል። አንተ በዮሴፍ ቦታ ብትሆን ምን አይነት ትግልና ጭንቀት የሚኖርብህ ይመስልሃል?
3. በቁጥር 1-4 መሰረት ዮሴፍ ለፓጢፋራ ቤት ሃላፊ ለመሆን የበቃው እንዴት እንደነበረ አስረዳ።
4. ቁጥር 5-6 ትን በማንበብ ዮሴፍ በዚህ ሰው ቤት ውስጥ በሃላፊነት የመሾሙ ውጤት ምን እንዳስከትለ ተናገር።
5. ቁጥር 7-9 በማንበብ ስለ ዮሴፍ ባህርይ ምን ምን ነገሮችን ማየት እንችላለን?
6. በተለይ በፖጢፋራ ሚስት በኩል የመጣውን ፈተና ከባድ የሚያደርጉ ምን ነገሮችን ትመለከታለህ?
7. ቁጥር 7-12 ስናነብ የዮሴፍ ፈተና በቀላሉ የማይወገድ እንደሆነ ይታያል። አንተስ አልወገድ ብሎ የሚያስቸግርህን ፈተና ለመወጣት ከዮሴፍ ምሳሌነት ምን ትማራለህ?
8. ዮሴፍ ለእግዚአብሄር ለመገዛት መቁረጡ ያስከፈለው ክፍያ ምን ነበረ? አንተስ ለእግዚአብሄር መታዘዝ ምን ያህል ክፍያ ለመክፈል ተዘጋጅተሃል?
9. ዮሴፍ የሰዎች በአካባቢው መኖር ሳይሆን ለአምላኩ ታማኝ ለመሆን በመወሰን ፈተናውን እንዳለፈ አንተም በሚገጥሙህ ማናቸውም ፈተናዎች አምላኬን እንዴት እበድላለሁ በማለት ዋጋ ለመክፈል ቁረጥ ጌትም ፀጋውን ያበዛልሃል።

# <u>ጥናት አምስት (ዘፍጥረት 22፥1-19)</u>

**የጥናቱ ዓላማ፡- የአብርሃምን እምነትና ህይወቱን በመመልከት እኛም በአምላካችን ላይ ሊኖረን የሚገባውን እምነታችንን ለማበረታታት።**

**የጥናት መክፈቻ፡- ነገሩ ከእግዚአብሄር መሆኑን እያወቅህ ለእግዚአብሄር ለመታዘዝ የሚያስቸግርህ ጊዜ አለ ወይ?**

1. **ዘፍጥረት 22፥1-19 በአንድነት ይነበብ። እግዚአብሄር በጣም የምትወደውን ሰው ከአንተ ሊወስደው ቢፈልግ ምን ዓይነት ስሜት ይሰማሃል?**
2. **ቁጥር 1-2 በማንበብ የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ ለአብርሃም የበለጠ ከባድ የሚያደርጉት ሁኔታዎችን ተናገር።**
3. **በዘፍ 17፥15-22 ያለውን በማንበብ ለአብርሃም ይህ ትዕዛዝ ለመታዘዝ የበለጠ አስቸጋሪ የሚሆንበትን መንገድ ግለጽ።**
4. **በቁ 1-10 ላይ አብርሃም እምነቱን ያረጋገጠባቸውን ሃሳቦች ዘርዝር።**
5. **የአብርሃምን ልምድ በማየት እምነት የሚለውን ሃሳብ እንዴት ትረዳዋለህ ወይም ትተረጉመዋለህ?**
6. **ቁጥር 15-18 ትን ስታነብ የአብርሃም እምነት ከራሱ አልፎ የሌሎችንም ሰዎች ህይወት የሚነካው እንዴት ነው።**
7. **አብርሃም በዚህ ፈተና ውስጥ ስለ እግዚአብሄር ምን አይነት ትምህርትን እንደተማረ ትገምታለህ? አንተስ ከዚህ ሰው ህይወት ምን ትማራለህ?**
8. **የአብርሃም ምሳሌነት በህይወትህ እግዚአብሄርን በበለጠ እንድታምነው ምን ያህል ይረዳሃል?**

## ጥናት ስድስት (ኤፌሶን 4፥17-5-7)

***የጥናቱ ዓላማ፡- ወደ ቅድስና ሕይወት እንደተጠራን በመረዳት ወደዚህ ዓይነቱ ሕይወት ለመድረስ በአዕምሮአችን መታደስ መለወጥ እንደሚኖርብን ለመማር።***
***የጥናት መክፈቻ፡-***

1. ኤፌሶን 4፥17-5፥7 በአንድነት ይነበብ። በቁጥር 17-19 ላይ ጳውሎስ ስለአህዛብ ይናገራል። ስለ አስተሳሰባቸው፥ አኗኗራቸውና ስለልባቸው በምን ዓይነት ነው የሚገልጸው?
2. የኤፌሶን ክርስትያኖች በቁጥር 20-24 ላይ እንዴት እንዲኖሩ ነው የሚመክራቸው?
3. በቅድስና በጽድቅ ሁሉ እግዚአብሄርን መምሰል ካስፈለገ ለምን ይመስልሃል በአዕ ምሮ መታደስ የሚያስፈልገው? ቁ 23
4. በተጨባጭ ሁኔታ በአዕምሮ መታደስ ማለት ምን ማለት ነው? ምሳሌ በመስጠት ለማስረዳት ሞክር።
5. በክርስቶስ ካገኘነው ማንነት የተነሳ አውልቀን መጣል ያለብንና በዚያ ምትክ ደግሞ መልበስ ያለብንን ነገሮች ዘርዝር። ቁጥር 25-32
6. በ5፥1-2 መሰረት ከሰዎች ጋራ በምናደርገው ግንኙነት እንዴት ነው ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰላችንን የምናሳየው?
7. ለምንድነው እንደ እግዚአብሄር ሰዎች በ5፥3-4 የሰፈሩትን ነገሮች ማድረግ ለክርስትያን ተገቢ የማይሆነው?
8. ከላይ በተማርከው መሠረት በህይወትህ መለወጥ ያለብህ ነገር ምንድነው? ለመለወጥ ውሳኔ አድርግ በራስህ ደግሞ ስለማትችል ለጌታ በጸሎት አቅርብ።

# <u>ጥናት ሰባት (ሉቃስ 10፥25-37)</u>

***የጥናቱ ዓላማ፡- የርህራሄን ይርጉም ከመጽሐፍ ቅዱስ በመመልከት እንደ ክርስትያን በርህራሄ መመላለስ እንደሚኖርብን ለመማር።***

***የጥናት መክፈቻ፡- ለሰዎች ችግር ለመድረስና በርህራሄው የምታደንቀው ሰው አለ ወይ? ስለዚያ ሰው ጎልቶ የሚታየው ነገር ምንድነው?***

1. **ሉቃስ 10፥25-37 በአንድነት ይነበብ። በራስህ ቃላት የመልካሙን ሳምራዊ ታሪክ ለመግለጽ ሞክር።**
2. **በቁጥር 25-29 ስለዚህ የህግ አዋቂ የምታያቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው?**
3. **ህግ አዋቂው ዘዳግም 6፥5, ዘሌ 19፥18 ይጠቅሳል። እነዚህ ሁለት ህግጋት እግዚአብሄር ከሰው የሚፈልገውን ነገር እንዴት ነው የሚያጠቃልሉት?**
4. **ኢየሱስ "ባልንጀራዬ ማነው" ለሚለው ጥያቄ የተናገረው ታሪክ (ቁ 30-35) በዚህ ዘመንስ ተመሳሳይ የሆነ ነገር ማሰብ ትችላለህ ወይ?**
5. **ካህኑና ሌዋዊው ሳይረዱ ያለፉበትን ምክንያት መገመት ትችላለህ ወይ? እኛስ በዚህ ዓይነት የምናልፋቸው ሰዎች ያሉ ይመስልሃል?**
6. **ሳምራዊው ያደረጋቸውን ነገሮች (ቁ 33-35) ዘርዝር። አይሁድና ሳምራውያን ካቅቸው ግንዝኙነት ጋራ ሲታይ የዚህ ሰው አድራጎት አስደናቂ የሚሆነው ለምንድነው?**
7. **የሳምራዊው አድራጎት የህግ አዋቂውን አመለካከት እንዴት የለወጠ ይመስልሃል? ቁጥር 36-37**
8. **በአንተ ህይወትስ የሰዎችን ጉዳት ለማየትና ለመረዳት የሚያግድህ ነገር ምን ይመስልሃል? በሌሎች ጉዳት ውስጥ ገብተን መስዋዕት የምንከፍል ሰዎች እንድንሆን በአንድነት ጌታን እንጠይቀው።**

## ጥናት ስምንት (ፊሊጵስዩስ 2፥1-30)

የጥናቱ ዓላማ፡- መጽሐፍ ቅዱስ ሌሎችን ዝቅ ብሎ ማገልገል ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ለመማርና እኛም ይህንን አይነት የአገልግሎት ዓይነት ለማገልገል ለማነቃቃት።
የጥናት መክፈቻ፡- ባርያ የሚለውን ቃል ስትሰማ ወደ አዕምሮህ ቶሎ የሚመጣው ሐሳብ ምንድነው?

1. ፊሊጵ 2፥1-30 በአንድነት ይነበብ። በዚህ ክፍል መሠረት ኢየሱስን፥ ጢሞቲዎስንና አፍሮዲጡን አንድ የሚያደርጋቸው ሓሳብ ምንድነው?
2. በቁጥር 3-4 ያሉት ትዕዛዛት ከሰው የተፈጥሮ ፍላጎት ጋራ ሲተያዩ ተቃራኒ የሚሆኑት በምን ዓይነት ነው? ከህብረተሰቡ አመለካከት ጋራስ?
3. ክርስቶስ ለእነዚህ ነገሮች ተወዳዳሪ የሌለው ምሳሌ የሚሆነን በምን መንገድ ነው?
4. ክርስቶስ ኢየሱስ እንደ ባርያ ለመሆን ያስከፈለው ነገር ምንድነው? ቁ 6-8
5. በቁጥር 20-21 ጢሞቲዎስን ከሌሎች ጋራ ያነፃጸረበትን መንገድ አስረዳ።
6. ጢሞቲዎስ በዚህ ዘመን ቢኖር ለክርስቶስ ያለውን መጨነቅ በምን ተጨባጭ በሆነ መንገድ ይገልጽ እንደነበረ ታስባለህ?
7. በቁ 25-30 መሠረት የአፍሮዲጡን ለጳውሎስና ለፊሊጵስዩስ ሰዎች ያሳየውን አገልግሎት አይነት በራስህ አነጋገር አስረዳ።
8. አንተ እያገለገልክ ያለኸውን አገልግሎት ከጢሞቲዎስና ከአፍሮዲጡ አገልግሎት ጋራ ስታነፃጽር እንዴት ትመዝነዋለህ? ከእነርሱስ አገልግሎት ምን ትማራለህ?
9. በአሁን ጊዜ በአገልግሎት ላይ ካልተሰማራህ ደግሞ የእነዚህ የሁለት ሰዎች ህይወት ጌታን ለማገልገል በምን ዓይነት ያነቃቃሃል?

## ጥናት ዘጠኝ (ዘጸዓት 3፥1-15, 4፥1፥17)

የጥናቱ ዓላማ፡- እግዚአብሄር ከእኛ ጋራ እስከሆነ ድረስ ማናቸውንም እግዚአብሄር የሚሰጠን ሃላፊነት መወጣት እንደምንችል ለመማር።
የጥናት መክፈቻ፡- ለምን ይመስልሃል አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች ከቤተክርስትያን ሃላፊነት መቀበልን የሚፈሩት? በራስህ ህይወትስ ይህ ዓይነቱ ልምድ ካለህ አካፍል።

1. ዘጸ 3፥1-15 እና 4፥1-17 በአንድነት ይነበብ። በዘጸ 3፥1-3 ውስጥ የምታየው ምን እንደሆነ ግለጽ።
2. ዘጸ 3፥4 ላይ እግዚአብሄር ሙሴን በስሙ ሲጠራው ይታያል። ይህ በእግዚአብሄር መታወቁ ለሙሴ ምን ስሜት እንደሚያመጣበት ይመስልሃል?
3. ዘጸ 3፥11-15 እና 4፥1 ሙሴ ወደ ፈርዖን እንዳይሄድ ሶስት ምክንያቶችን ያቀርባል። እነዚህ ምክንያቶች ሙሴ ስለራሱና ስለ እግዚአብሄር ስላለው አመለካከት ምን ያሳያሉ?
4. ከላይ በተመለከትናቸው የሙሴ ምክንያቶች እግዚአብሄር በምን መንገድ ነበረ ሙሴን ሊያበረታታው የቻለው?
5. ዘጸ 4፥10 ሙሴ እግዚአብሄርን ማገልገል የማይችልበትን የራሱን ምክንያት ሲያቀርብ የእግዚአብሄር አመለካከት ስለሙሴ በምን መንገድ የተለየ ይመስልሃል? ዘጸ 4፥11-12
6. በዘጸ 4፥13 መሰረት መቼ ነው ስለራሳችን የሚኖረን ዝቅተኛ አመለካከት በእግዚአብሄር ፊት ሃጥያት የሚሆነው?
7. ሙሴ ላቀረባቸው ምክንያቶች እግዚአብሄር የሰጠው መልሶች ወደፊት ከጌታ ሃላፊነትን ለመቀበል በግልህ ምን ያህል ማበረታቻ ሆነውሃል?
8. እግዚአብሄር ሊሰጥህ የሞከረውና አንተ በእንቢታ ያሳለፍከው ሃላፊነት ካለ በጌታ ፊት ንስሃ በመግባት፥ በጸሎትና በመታዘዝ ሁኔታውን ዛሬ አስተካክል።

# <u>ጥናት አስር (1ኛቆሮ 12፥4-26)</u>

*የጥናቱ ዓላማ፡- የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የክርስቶስን አካል ለማነጽ ያላቸውን ከፍተኛ ሥፍራና አስፈላጊነታቸውን እንድናይና በሚገባ እንድንጠቀምባቸው ለማበረታታት።*
*የጥናት መክፈቻ፡- መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ለቤተክርስትያን ባይሰጥ ቤተክርስትያን አሁን ካለችበት ሁኔታ በምን መንገድ የተለየች ትሆን ይመስልሃል?*

1. 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥4-26 በአንድነት ይነበብ። ከሰውነታችን ክፍል አንዱ ብልት በትክክል ባይሰራ አካላችን በምን ሁኔታ ይጎዳል ትላለህ?
2. በቁጥር 4-11 መሰረት ስለ ስጦታዎች መመሳሰልና ብሎም ደግሞ መለያየት ምን ትመለከታለህ?
3. ስጦታዎቹ የተሰጡበት ዓላማ ምንድርነው?
4. በቁጥር 15-16 ላይ ጳውሎስ ማረም ወይም ማስተካከል የፈለገው የተሳሳተ አመለካከት ምን ይመስልሃል?
5. ቁጥር 21-33 ባለው ክፍል ሃዋርያው እያንዳንዳችንን እንዴት እንድንተያይ ነው የሚያስተምረን?
6. በቁጥር 14-26 ባለው ክፍል የምናነበው ሃሳብ ከፍ አድርገን ስለምናያቸውና አሳንሰን ደግሞ ስለምናያቸው ብልቶች(ወገኖች) ምን ያስተምረናል?
7. አንተስ ራስህን በአካሉ ውስጥ ስትመለከተው የዝቅተኛነት ወይም የከፍተኛነት ስሜት ተሰምቶህ ያውቃል ወይ? ሌላውንስ በዚህ ዓይነት የተመለከትክበት ጊዜ ታስታውሳለህ ወይ?
8. በ 12፥7 መሠረት እያንዳንዱ ክርስትያን አካሉን ለማነጽ ስጦታ ተሰጥቶታል። አንተስ በተሠጠህ ስጦታ አካሉን በማነጽ ላይ ነህ ወይ? ካልሆነ በጌታ ፊት ንስሃ በመግባት በተሰጠህ መክሊት ለመሥራት ወስን።

## ጥናት አስራ አንድ (ማርቆስ 10፥32-45)

የጥናቱ ዓላማ፡- መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ትክክለኛውን ትህትና ምን እንደሆነ በመረዳት ከትዕቢት ህይወት ለመራቅ።

የጥናት መክፈቻ፡- ሰው ስለራሱ የተሳሳተ አመለካከት ማለትም ዝቅተኛነት የሞላበት አስተሳሰብ በመያዝና በትህትና መካከል ያለውን ልዩነት ግለጽ።

1. ማርቆስ 10፥32-45 ያለው በአንድነት ይነበብ። በዚህ ክፍል በኢየሱስና በሁለቱ ወንድማማቾች መሃል የተፈጠረው አነጋጋሪ ሁኔታ ምን ነበረ?
2. 10፥32-34 ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሚነግራቸው ነገር ምን ነበረ? በዚህስ መሠረት የሁለቱ ወንድማማቾች ጥያቄ የማይገባ የሚሆነው ለምን ይመስልሃል?
3. ራስህን አንዳንዴ እንደ ያዕቆብና ዮሃንስ ሆነህ የምታገንበት ጊዜ አለወይ?
4. ቁጥር 41 ላይ የምታየውን የአስሩን ደቀ መዛሙርትና የሁለቱን ወንድማማቾች ሃጥያት አነጻጽር።
5. በቁጥር 42-45 ውስጥ ኢየሱስ በዓለምና በእግዚአብሄር መንግስት ስለ ትልቅነት ያለውን የአመለካከት ልዩነት በምን ዓይነት ነው የሚገልጸው?
6. በዚህ ዘመንስ ክርስትያኖች ትልቅነትን በተመለከተ የዓለምን ዓይነት አመለካከት የምንይዝባቸውን አንዳንድ ምሳሌዎች በመስጠት አስረዳ።
7. በቤተ ክርስትያን፥ በሥራህ፥ ወይም በቤትህ የትህትናን ትክክለኛ ሞዴል ያየህበትን ሁኔታ አስረዳ። የአንተስ ህይወት ስለትህትና በአካባቢህ ላሉት ሰዎች ምን ያስተምራል?
8. ጌታ ኢየሱስ ስለትልቅነት ይስተማረው አመለካከት የህይወትን አቅጣጫ ሁሉ የሚነካ ነው። ከዚህ አንጻር ጌታ እንዲለውጥህ የምትፈልገውን በወገኖች ፊት በጸሎት አሳልፈህ ስጥ።

# ጥናት አስራ ሁለት (2ኛጢሞ 1፥8-2፥7)

የጥናቱ ዓላማ፦ በሰላምና በመልካም ዘመን ብቻ ሳይሆን ክርስትያን በመከራና በችግር ጊዜም ፀንቶ መቆም እንደሚኖርበት ለመማር።
የጥናት መክፈቻ፦ ነገሮች ከአቅምህ በላይ ሆነውብህ የክርስትናን ህይወት ያማረርክበት ጊዜ ነበረ ወይ?

1. 2ኛ ጢሞ 1፥8-2፥7 በአንድነት ይነበብ። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስለ ጳውሎስ፥ ጢሞቲዎስና ስለሁለቱ ግንኙነት ምን የምትመለከተው ነገር አለ?
2. ጢሞቲዎስ ከእርሱ ጋራ ለወንጌል መከራን እንዲቀበል ካደፋፈረው በኋላ በ1፥9-10 በተለይ ያተኮረባቸው እውነቶች ምንድናቸው?
3. ጢሞቲዎስ ከፊቱ ሊጠብቁት ስለሚችሉት ነገሮች በ1፥13-14 የሚጠቁመን ሃሳብ ምንድነው?
4. ራስህን በጳውሎስ ቦታ አድርገህ በእስር ቤት፥ ብቻውን፥ ሰው ሁሉ ትቶት(ቁ15) ምን ዓይነት ሥሜት የሚሰማህ ይመስልሃል?
5. በቁጥር 16-18 ሄኔሲፎሩን የተለየ የሚያደርገው ነገር ምንድነው?
6. ጳውሎስን ከሚጠብቀው በቅርቡ የመሞት ነገር ጋራ ሲተያይ በ2፥2 የተፃፈውን ሃሳብ ይበልጥ ትኩረት እንዲሰጠው የሚያደርገው ምን ይመስልሃል?
7. በ2ኛ ጢሞ 2፥3-6 ባሉት ቁጥሮች ላይ ሶስት የደቀመዝሙርን ህይወት ለመግለጽ የጠቀሳቸው ነገሮች(ወታደር፥ትዳርና ገበሬ) በምን መንገድ እንደሚጠቅሙ ተወያዩባቸው።
8. የእምነት አባቱ መታሰሩና ለሞት መቅረቡ፥ ብዙዎችም ደግሞ ከወንጌል ፊቀቅ ማለታቸው ለጢሞቲዎስ ትልቅ ተስፋ አስቆራጭ ነገር ነው። 2ኛ ጢሞ 2፥1 ለዚህ ሰው ምን አይነት ማነቃቂያ ይሆነዋል ትላለህ? ለምን?
9. ሁኔታዎች ሁሉ የማያምሩ ሲሆኑ አንተንስ የክርስቶስ ኢየሱስ ጸጋ መኖር ምን ያህል በአገልግሎትህ ለመጽናት ያነቃቃሃል? ጌታ ለአገልግሎት ጸጋን ስለሰጠን ልናመሰግነው ይገባናል።